**እስራኤል አገር**
**የትምህርት ሚኒስቴር**
የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና
የፈተናው ጊዜ፦ የ2018 ዓ.ም. የበጋ ፈተና
**የፈተናው ቁጥር፦ 029284**
አባሪዎች፦ አባሪ ለጥያቄ 6 (አዋጅ)
አባሪ ለጥያቄ 7 (አዋጅ)
**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የሃይማኖት ታሪክ
## ለአዲስ ገቢዎች
### በሃይማኖተኞች ት/ቤቶች ለሚማሩ

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

א. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎችን ይዟል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | (3x13) | — | 39 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | (1x22) | — | 22 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሦስት | (3x13) | — | 39 ነጥብ |
| በአጠቃላይ | | — | 100 ነጥብ |

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. ልዩ መመሪያ፦

በመልስህ ላይ ተጨባጭ እውነታዎችን አሳይ፥ ጠቅለል ባለ መልስ አታብቃ።

እንደ ንድፍ (טיוטה) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ የሒሳብ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ። በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ። ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

**מדינת ישראל**
**משרד החינוך**
סוג הבחינה: בגרות
מועד הבחינה: קיץ תשע"ח, 2018
**מספר השאלון: 029284**
נספחים: נספח לשאלה 6 (כרזה)
נספח לשאלה 7 (כרזה)
**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה דתי
## לעולים חדשים
### בבתי ספר דתיים

**הוראות לנבחן**

א. משך הבחינה: שעתיים וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה שלושה פרקים.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | (13x3) | — | 39 נקודות |
| פרק שני | (22x1) | — | 22 נקודות |
| פרק שלישי | (13x3) | — | 39 נקודות |
| סה"כ | | — | 100 נקודות |

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. הוראה מיוחדת:

בתשובתך הבא עובדות ואל תסתפק בהערכות כלליות.

כתוב במחברת הבחינה בלבד, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב כטיוטה (ראשי פרקים, חישובים וכדומה). רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (39 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)

**1.** ከእውቀቱ (נאורות) **መገለጫዎች** ውስጥ ሁለቱን **ጥቀስ**።
እነዚህ ሁለቱ የእውቀት መገለጫዎች በ"ሞሼ ሜንዴልሶን" ርዕዮተ ዓለም ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳደረጉ **አብራራ** (በአጠቃላይ ሁለት ማብራሪያዎች)።

**2.** የዘመናዊ ብሔርተኝነትን (לאומיות המודרנית) ዓላማ **አቅርብ**።
ከሚከተሉት ክስተቶች ውስጥ አንዱን ምረጥ፦ የአሜሪካ አብዮት (המהפכה האמריקנית) ወይም የፈረንሳይ አብዮት (המהפכה הצרפתית) ወይም የኢንዱስትሪ አብዮት (המהפכה התעשייתית) ወይም የብሔራዊ መነሣሣት (አብዮት) (אביב העמים)።
የመረጥከው ክስተት የዘመናዊ ብሔርተኝነት እንዲስፋፋ እንዴት ተጽዕኖ እንዳደረገ **አብራራ**።

**3.** የጺዮናዊያንን እንቅስቃሴ (התנועה הציונית) ዓላማ በ"ባሴል ዕቅድ" በታቀደው መሠረት **አቅርብ**።
የባሴልን ዕቅድ ለማካሄድ የተቋቋሙ ሁለት ተቋማትን **አቅርብ**።

**4.** ራብ ኩክ በአዲሱ ሠፈራ አቅኚዎች (חלוצים) ሰዎች ላይ የነበረው አቋም ምን እንደነበር **አብራራ**።
ራብ ኩክ ያቀደውን የራባናት ጉዞ (מסע הרבנים) (1913) ሁለት ዓላማዎች **አቅርብ**።

**5.** የባልፉርን አዋጅ ይዘት **አቅርብ**።
ይህ የባልፉር አዋጅ ለጺዮናዊያን እንቅስቃሴ ያለውን አስፈላጊነት **አብራራ**።

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሁለት (22 ነጥብ)

ከ6-7 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**6. נאציזם (ናዚነት)**

ኢ. በጥያቄ 6 አባሪ ላይ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ጀርመን ወደ ኮምኒስቷ (ቦልሸቪኳ) ሶቭዮት ሕብረት ሰብረው በገቡበት ወቅት ናዚዎች ያወጡት አዋጅ ቀርቧል።
በአዋጁ አማካኝነት የተገለጸውን የናዚዎች ርዕዮተ ዓለም አንድ ዋና ዓላማ **አቅርብ**።
ይህ ዋና ዓላማ እንዴት በዚህ አዋጅ እንደተገለጸ ከአዋጁ ውስጥ በሆኑ ሁለት ክፍሎች (רכיבים) መሠረት አብራራ። (11 ነጥብ)

ኔ. በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሰላሳኛዎቹ ዓመታት ውስጥ ናዚዎች በጀርመኖች ላይ ግዛታቸውን ለማደራጀት የተጠቀሙባቸውን ሁለት መንገዶች **አቅርብ**። (11 ነጥብ)

**7. העלייה הגדולה בתחילת שנות החמישים**
**(በአሥራ ዘጠኝ ሀምሳዎቹ መጀመሪያ ላይ በብዛት ወደ እስራኤል መግባት)**

ኢ. አገሪቱ ከተቋቋመች በኋላ ከእስላም ሃገራት ወደ እስራኤል አገር በብዛት ለመግባት (עלייה הגדולה) መንስኤ የሆነውን አንድ ምክንያት እና በዚሁ ወቅት ከአውሮፓ ወደ እስራኤል አገር በብዛት ለመግባት መንስኤ የሆነን ሌላ ምክንያት (በአጠቃላይ ሁለት ምክንያቶችን) **አቅርብ**። (11 ነጥብ)

ኔ. በጥያቄ 7 አባሪ ላይ አዋጅ ቀርቧል። ይህ አዋጅ የ"ኩር ሃሂቱሀ"ን (כור ההיתוך) መምሪያ ለማካሄድ የወጣ ነው።
የ"כור ההיתוך"ን መመሪያ **አቅርብ**።
የአዋጁ መልዕክት ምን እንደሆነ **ጥቀስ** እና የጠቀስከውን መልዕክት ሠዓሊው (አዋጁን የነደፈው) ከአዋጁ በሆኑ ሁለት ክፍሎች አማካኝነት እንዴት እንዳገላቸው **አብራራ**።
(11 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

## **ምዕራፍ ሦስት** (39 ነጥብ)

ከ8-12 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (እያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)።

**8.** የሪቤንትሮፕ-ሞሎቶብን (ריבנטרופ-מולוטוב) (1939) ስምምነት **አቅርብ** እና ይህም ለምን ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመር ምክንያት እንደሆነ **አብራራ**።
ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ለማቆም ያገዘ አንድ ክስተት **ጥቀስ**።

**9.** ከሄይድሪህ ኢጌሬት ሃባዛክ (איגרת הבזק) (1939) ንውሳን ውስጥ ሁለቱን **ጥቀስ**።
የናዚ ግዛት ፖላንድን ከወረረ በኋላ በይሁዳዊያን ላይ የጣለውን ሌላ ፍርድ **ጥቀስ**።

**10.** ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የሜሪ ሃዒብሪ የዕብራውያን አመጽ (מרי העברי) (1945) እንቅስቃሴ እንዲቋቋም ያደረገውን ምክንያት **አቅርብ**።
የሜሪ ሃዒብሪ እንቅስቃሴ ከአሥር ወራት በኋላ ብቻ ለምን እንደፈረሰ **አብራራ**።

**11.** በ"אייר תש"ח" (ግንቦት 1948) አገሪቱ ስትቋቋም አዋጁን የደገፈ አንድ ድምዳሜ **አቅርብ** እና በዚሁ ጊዜ አዋጁን የተቃወመ አንድ ድምዳሜ **አቅርብ**።

**12.** የነጻነቱ ጦርነት ካበቃ በኋላ በእስራኤል አገር እና በአረብ አገራት መካከል የተኩስ ማቆም ስምምነት ተፈረመ (1948)።
እስራኤል አገር የጦርነት ማቆም ስምምነት የተፈራረመቻትን አንዲት የአረብ አገር **ጥቀስ** እና ይህች አገር ለምን ይህን ስምምነት እንደፈረመች **አብራራ**።
እስራኤል አገር ለምን ከአረብ አገሮች ጋር የጦርነት ማቆም ስምምነት እንዳደረገች **አብራራ**።

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך

**ለጥያቄ 6 አባሪ — ማስታወቂያ**

ድል →




← ወይም

← ቦልሽቪኪዝም (ኮምኒዝም)

የማስታወቂያው ርዕስ ትርጉም፦ ድል ወይም ቦልሽቪኪዝም (ኮምኒዝም)

(http://www.dhm.de)

**ለጥያቄ 7 አባሪ — ማስታወቂያ**




(palestineposterproject.org)